## ተቋሙ የሚሰጣችሁ አገልግሎት

ተቋሙ ከምስረታ ዘመኑ ጀምሮ ጥራት ያለዉ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ፋስሊቶች ማለትምየመኝታ፣የመማሪያ፣የሻወርና የመጸዳጃ ቤቶች፣አደራሽ፣ካፍቴሪያ የመሳሰሉት ለስልጠናና ለሌሎች አገልግሎቶች ምቹ ባለመሆናቸዉ የሚያረካ አገልግሎት መስጠት አልተቻለም ነበር፡፡ ነገር ግን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን የተቋሙ አመራር እና የተቋሙ ቦርድ ተቋሙ ለሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ባለፉት ዓመታት በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተግዳሮቶች የነበሩትን የምግብ አገልግሎት ከዚህ በፍት በውጭ አካላት ሲሰራ የነበረውን የተለያዩ የምግብ ቤት ቁሳቁሶችን በመግዛት እና የምግብ ባለሙያ በመቅጠር በራሱ ጀምሮ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የሰልጣኞች የመኝታ ክፍሎች ፣የስልጠና ክፍሎች፣የሻወርና የመጸዳጃ ቤቶች፣ የምግብ ማብስያ ክፍሎች፤ካፍቴሪያ የመሳሰሉትን የማደስና ቁሳቁሶችን በማሟላት በተለይም በያዝነው የበጀት ዓመት ከዚህ በፊት ግንባታው ተጀምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ተቋረጦ የነበረው የሰልጣኞች ማደረያ ክፍል ከኮንትራክተሩ ጋር በመነጋገር በህጉ መሰረት ውሎ ተቋርጦ ግንባታውን ለመጀመር ከከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ቢሮ ጋር በመሆን ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ለብዙ ዘመናት በተቋሙ እና በተገልጋዮች ዘንድ እንደ ችግር ሲነሱ የነበሩ ጉዳዮች ማለትም የተቋሙ አጥር እና መሰብሰብያ አዳረሽ ግንባታ ለማካሄድ የዲዛይን እና የጨረታ ስራዎች ተጠነቀው ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ተቋሙ የስልጠና ማዕከል እንደመሆኑ መጠን ግቢውን ውብ እና ማራኪ ከማድረግ አንጻር ብዙ ስራዎች በመሰራት ላይ የሚገኝ ቢሆንም ከዚህ ባለፈ ደግሞ ተቋሙ ከተመሠረቱበት ዓላማ አንፃር የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እና ቀጣይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ በአግባቡ እንዲወጣ

ለማድረግ በተቋሙ የሚሰጡ አግልግሎቶችን ለማዘመን የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም በተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ማነቆ ከሚፈጥሩ ችግሮች ዋነኛው በጉዞ ላይ የሚደረጉ ብክነቶች መሆናቸው በዳሰሳ ጥናት እንዲሁም በተግባር በተደረገ ክትትል የታወቀ ሲሆን ሰራተኘው በመመላለሱ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ሰዓት እና ከፈተኛ የሆነ የነዳጅ ወጪ ብክንት በማስከተሉ ከዚህ በላይግን በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጫና በመጠሩ በተቋሙ የሰራተኞች ክበብ በማደራጀት ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም በሀገራችን ብሎም በክልላችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ መንግስት የልማቱ ዋና መሪ፣ አንቀሳቃሽና ተዋናይ በመሆኑ ቀጣይነት ያለው መዋቅራዊ ለዉጥ እንቅስቃሴ እውን ለማድረግ በአመለካከት፣ በዕዉቀትና በክህሎት ብቃት ያለው አመራርና ፈፃሚ ሀይል በማፍራት የመንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በአግባቡ እና በብቃት የሚያስፈፅምና የሚፈፅም የመንግስት ተቋማትን በማብቃት ሀገራዊና ክልላዊ ተልዕኮ ለማሳካት ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ሥራዎችና የጥናትና ምርምር ተግባራት ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህ ተግባርና ዓላማ ስኬታማነት የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ሥራ አመራር ተቋም ትልቅ ሀላፊነት የሚጠበቅበት በመሆኑ የተቋሙን ተልዕኮ እና ራዕይ መነሻ ያደረገ በዉጤት ተኮር ሥርዓት በተቃኘ መልኩ የሰስተኛዉን የዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ ሆኖም አሁንም ቢሆን በአገልግሎት አሠጣጥ ዙሪያ የተገልጋዩን አመኔታና እርካታ ማሟላት የሚያስችል ቁመና ከመያዝ አንጻር የሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብና ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡ አስተያየት ከመስጠት ጀምሮ ፋሲሊቲ ለማሟላት የቁሳቁስ፣ የሀሳብና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣ በተለይም ደግሞ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በክልሉ መንግስት የተላለፈውን መመርያ መሰረት በማድረግ በተቋሙ ስልጠናዎችን በመስጠት እና ሌሎች አገለግሎቶችን በመጠቀም ዕገዛ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት፣ከተገልጋዮች እና አቻና አጋር ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነትን በተመለከተ፡-**

ተቋሙ ከአቻና አጋር ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ሁኔታ ማለትም ከአሶሳ ዩኒቨርስቲ፣ ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፣ከኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ ፣ከኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት፣ ከአማራ አመራር አካዳሚ ጋር የጋራ የስምምነት ሰነዶችን መፈራረም የተቻለ ሲሆን ከአንዳንዶቹም ጋር ዕቅድ ታቅዶ ወደ ተግባር ለመግባት የተሞከር በተፈራረምነው ልክ ግን ተቀናጅቶ ዉጤታማ ስራን ከመስራት አንፃር ግን ክፍተት አለበት፡፡ እንዲሁም ተቋሙ ከተገልጋዮችና ከባለድረሻ አካላት ጋር ያለውን አጋርነትና ግንኙነትን ይበልጥ ለማጠናከር እንዲሁም የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ፣ የተቋሙን ገጽታ ለማስተዋወቅ እና ገንቢ አስተያየቶችን ከተቋሙ ተገልጋዮችና ባለድረሻ አካላት ለመዉሰድ በየጊዜዉ ከተቋሙ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ጋር ዉጤታማ የሆነ የምክክር መድረኮችን ሲያካሂድ የቆየ ቢሆንም በታቀደዉ መሠረት ባለመሆኑ በቀጣይ ታቅዶ ሊሰራበት ያስፈልጋል ፡፡